# 2024–2025
# የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ ለማድረግ (COSA)
## የመረጃ መጽሔት

### መግለጫ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች በተመደበላቸው የመኖሪያ አካባቢ ት/ቤት ወይም ባለባቸው ግላዊ ሁኔታ ምክንያት በተመደ ቡበት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይጠበቃል። ተማሪዎች ከአካባቢ ት/ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም IEP ሂደት ምክንያት ከተመደቡበት ት/ቤት በሚከተሉት መመዘኛዎች/መስፈርት መሠረት ወደ ሌላ ት/ቤት ለመቀየር (COSA) ማመልከት ይችላሉ፡-

- ልዩ ችግር–ተማሪዎች ከአካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነታቸው ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ወይም የቤተሰባቸውን ግላዊ ሁኔታ በትምህርት ቤት የምደባ ለውጥ ሊቃንስላቸው በሚችልበት ጊዜ COSA ማመልከት ይችላሉ።
- የቤተሰብ ከአካባቢ መዛወር––ቤተሰቦቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቦታ የሚቀይሩ ተማሪዎች በቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ለመቀጠል የሚፈልጉ ተማሪዎች ምንም የተለየ ምክንያት ሳያቀርቡ COSA ሊጠይቁ ይችላሉ። እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ለወቅቱ የትምህርት ዘመን ቀሪ ጊዜ ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ከዚህ በተለይ በ 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው እስከሚመረቁ እንዲቆዩ COSA ይሰጣቸዋል።
- እህት/ወንድም– ተማሪ መመዝገብ በሚፈልግበት አመት ወንድም/እህት በመደበኛው የት/ቤት ምደባ ወይም በልዩ ትምህርት ፕሮግራም የሚመዘገብበት ትምህርት ቤት ከሆነ።
    - » ወንድም ወይም እህት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማግኔት፣ የቋንቋ ኢመርዥን የሚማሩ ከሆነ ወይም ሌላ በማመልከት ላይ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶችን እንደየጉዳዮ ሁኔታ COSA በቋሚነት ወደሚሰጠው የትምህርት ቤት ፕሮግራም እንዲገቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል። የዚህ አይነት ፈቃድ በመማርያ ክፍል ቦታ የመኖር፣ የክፍል-ደረጃ ምዝገባ፣ የሰራተኛ አመዳደብ፣ ወይም በሚመለከታቸው ት/ቤቶች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ታሳቢዎች ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለባቸው።

የት/ቤት ማካለል ለውጥ ከተደረገ ወይም ወንድም/እህት በቅድመ መዋእለ ህጻናት (PreK) ውስጥ ካለ(ች) ከላይ የተጠቀሱት መመዘኛዎች አይተገበሩም።

ለተጨማሪ አማራጮች COSA ቅጽ ይመልከቱ

---

እነዚህ ተማሪዎች የጋራ ክልል ውስጥ ሌላ ትምህርት ቤት ለመግባት ከጠየቁ COSA ማስገባት የለባቸውም፡-

- በኖርዝኢስት ክልል ዞርያ (NEC) ወይም ዳወንካውንቲ ክልል ዞርያ (DCC) የሚኖሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሌላ ክልል ት/ቤት የሚጠይቁ ከሆነ።
- በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም (MSMC) የሚኖሩ የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ሌላ የመካከለኛ ደረጃ ማግኔት ኮንሰርሽየም "MSMC" የሚጠይቁ ከሆነ ወይም በ MSMC የምልመላ ሂደት እጣ የተሳተፉ እና ለ MSMC ትምህርት ቤት የሚያመለክቱ ተማሪዎች።
- በኮንሰርቲየም ውስጥ ያለ ሌላ ትምህርት ቤት የሚጠይቁ ከሆነ፣ DCCAPS ለኮንሶርሺያ ምርጫ እና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል (DCCAPS) በኢሜል እና የተፈረመ የጽሁፍ ይግባኝ ደብዳቤ ማቅረብ አለብዎት። @mcpsmd.org፣ 11721 Kemp Mill Road፣ Silver Spring፣ Maryland 20902 NEC፣ DCC ወይም MSMC ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ስለመቀየር መረጃ ለማግኘት DCCAPS በስልክ ቁጥር 240-740-2540 ያግኙ ወይም ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice

---

እባክዎ ያስታዉሱ፡- የአደጋ ክስተት ከሌለ፣ ሁሉም COSA ጥያቄ ኤፕሪል 2, 2024 መቅረብ አለበት፣ እና COSA የተቀበሉ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች መጓጓዣ ማቅረብ አለባቸው።

ተማሪ በሞግዚትነት የሚያስተዳድሩ ሠራተኞች እና የእንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍል (DPPAS)
240-740-5620 • COSArequest@mcpsmd.org

MONTGOMERY COUNTY
Board of Education
MARYLAND

## VISION
## ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ መማርን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉንም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው እንዲዳብር/ እንዲበለጽግ ማዘጋጀት፡፡

## ዋነኛ እሴቶች

መማር/እውቀት
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት


Board of Education የትምህርት ቦርድ

Ms. Karla Silvestre ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ
Presidentፕ ሬዚደንት

Ms. Lynne Harris ሚ/ስ ለይኔ ሃሪስ
Vice President ም/ፕሬዚደንት

Mrs. Shebra L. Evans ወ/ሮ ሸብራ ኤል. ኢቫንስ

Ms. Grace Rivera-Oven ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን

Mrs. Rebecca K. Smondrowski ወ/ሮ ርብቃ ኬ. ስሞንድሮውስኪ

Ms. Brenda Wolff ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ

Ms. Julie Yang ሚ/ስ ጁሊ ያንግ

Mr. Sami Saheed አቶ ሳሚ ሰዒድ
Student Member ተማሪ አባል

Montgomery County Public Schools (MCPS)
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Administration አስተዳደር

Monifa B. McKnight, Ed.D. ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
Superintendent of Schools የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

Mr. M. Brian Hull ሚ/ር ኤም ብራያን ሃል
Chief Operating Officer ዋና ሥራ አስኪያጅ

Dr. Betty J. Collins ዶክተር ቤቲ ጄ. ኮሊንስ
Acting Deputy Superintendent of Schools
የት/ቤቶች ተጠባባቂ ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

Mrs. Stephanie P. Williams ወይዘሮ ስቴፋኒ ፒ. ዊሊያምስ
General Counsel ጀነራል ካውንስል

Ms. Elba M. Garcia ሚስ ኤልባ ኤም ጋርሺያ
Senior Community Advisor የማህበረሰብ ከፍተኛ አማካሪ

Dr. Patricia E. Kapunan ዶክተር ፓትሪሺያ ኢ ካፑናን
School System Medical Officer የትምህርት ቤቶች የጤና መኮንን



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

## በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

**ት/ቤት ለመቀየር እንዴት ማመልከት እችላለሁ?**

MCPS ቅጽ 335-45: የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ ጥያቄ፣ በዚህ የመረጃ መጽሔት/ቡክሌት ውስጥ ተካትቷል። ቅጹ በሰባት ተጨማሪ ቋንቋዎች ጭምር በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፦ www.montgomeryschoolsmd.org/info/transfers/ ቅጹን ሞልተው ለግምገማ የነዋሪነት ማረጋገጫው ጋር ለርእሰ መምህሩ ፊርማ ወደ ትምህርት ቤትዎ ይመልሱ። አድራሻ ሲለወጥ አዲሱን የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ (የጋራ መኖሪያ ቤት ቅፅ/ሊዝ/የተፈረመበት መግለጫ) ይዘው ይምጡ። ት/ቤቱ ቅጹን/ማመልከቻውን ለማካሄድ(ለማስፈጸም) ወደ DPPAS ይልካል።

ለት/ቤት ስርአት አዲስ የሆኑ ተማሪዎች COSA ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በአካባቢያቸው ት/ቤት መመዝገብ አለባቸው። COSA ጥያቄዎች ተማሪው/ዋ የመኖርያ ማረጋገጫ እና የምዝገባ ሂደት በአካባቢ ት/ቤት እስኪ(ክት)ፈፅም ድረስ አይታዩም/አይገመገሙም።

**ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?**

2024-2025 የትምህርት አመት COSA ማመልከቻዎች ፌብሩዋሪ 2024 የመጀመሪያው የትምህርት ቀን እና ኤፕሪል 2024 የመጀመሪያው የትምህርት ቀን መካከል መቅረብ አለባቸው። ስለቀረቡት COSA ጥያቄ እስከ ሜይ 24/2024 ድረስ ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ውሳኔውን ለማሳወቅ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን። ከኤፕሪል የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በኋላ የሚቀርቡ COSA ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ተማሪው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ አዲስ ነዋሪ ከሆነ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) የመኖሪያ አድራሻ(ዋ)ውን ከቀየረ(ች) ወይም ከኤፕሪል በፊት ሊተነበይ የማይቻል ድንገተኛ ክስተት ከኖረ ብቻ ነው። ይህን ሁኔታ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ መቅረብ አለበት። ሰነዱ ከኤፕሪል ማብቂያ ቀን በኋላ የተከናወነውን የቤተሰብ እንቅስቃሴ ወይም ጉልህ የሆነ ከትምህርት ቤት ወይም ከማህበረሰብ ጋር የተያያዘ ክስተትን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። COSA አመልክተው ዉሳኔ በመጠበቅ ላይ ያሉ/የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት መከታተል አለባቸው።

**COSA ሳመለክት በአባሪነት ማቅረብ ያለብኝ ማስረጃዎች ምንድናቸው?**

በእርስዎ ግላዊ ሁኔታ ይወሰናል፣ ነገር ግን፣ ሰነዶች በተናጥል ሊረጋገጡ የሚችሉ እውነታዎችን መያዝ አለባቸው። ለምሳሌ፦ የፋይናንስ ማስረጃዎችን፣ ከጤና ባለሙያዎች የተጻፉ ደብዳቤዎች፣ እና ከአሠሪዎች/ቀጣሪዎች የሚጻፉ ደብዳቤችን ያካትታል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል።

**ልዩ ችግር ማለት ምንድን ነው?**

ልዩ ችግር በቤተሰብ ግላዊ እና ግለሰባዊ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ነው። በአብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ዘንድ የጋራ የሆኑ ችግሮች ለምሳሌ፦ የህፃናት መዋያ/ዴይኬር፣ ወይም የፕሮግራም/የኮርስ ምርጫ፣ የመጓጓዣ ጉዳዮች ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር እንደ ከባድ ችግር-እንግልት ተደርገው አይቆጠሩም። ሁሉም የችግር ጥያቄዎች በተናጠል ሊረጋገጥ የሚችል ሰነዳ አባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣ አለዚያ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል። እንደዚህ ያሉ የልዩ ችግር ምሳሌዎች፣ በዚህ የሚወሰኑ ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፦

- የህፃናት እንክብካቤ: ወላጆች/አሳዳጊዎች እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሠዓት በፊት እና/ወይም ከትምህርት በኋላ ከዕድሜ ጋር የሚስማማ ክትትልን ሲደረግ የማይመቻቸው ሁኔታዎች ካሉ መግለጽ አለባቸው፦ (a) የሥራ ሰዓታቸው በቤት አካባቢ ለሚገኙት ት/ቤቶች የልጆች እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ከሚሰጠው ዓይነተኛ ሰዓት በላይ ወይም በቀላሉ ሊደረስባቸው የሚችሉ የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች ላይ በእጅጉ የሚራዘም ይሆናል፤ እና/ወይም (b) ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ደግሞ ቤተሰቡ የልጆችን እንክብካቤ በሌላ መንገድ የማግኘት ችሎታቸውን ይገድባል ወይም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የተማሪዎችን ፍላጎት ይገድባል። የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ባሻገር ላሉ ተማሪዎች እጅግ በጣም ወሳኝ/ትርጉም ያለዉ መሆን አለበት።
- የተማሪን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነትን የሚመለከቱ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ። በዚህ ምክንያት COSA የሚጠይቁ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለባቸው ፦ (a) ከተማሪ አካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በቀጥታ ከትምህርት ቤቱ ሁኔታ ጋር የተገናኙ ወይም ጉልህ ተፅእኖ ባላቸው ጉዳዮች በጤና አጠባበቅ ባለሙያ አማካይነት ቀጣይነት ያለው ህክምና የሚደረግ ከሆነ፣ እና/ወይም (b) የተለየ የእንክብካቤ መስፈርቶች ያለው ጉልህ የጤና ጉዳይ (ለምሳሌ፦ ተደጋጋሚ የህክምና ቀጠሮ ለመያዝ ከተማሪ የአካባቢ ትምህርት ቤት እና/ወይም የወላጅ/አሳዳጊ የስራ ቦታ የተራራቀ ከሆነ)።

**ልጄ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እየተከታተለ(ች) ቢሆንስ?**

የተማሪዎ በግላይ ሁኔታ ላይ ተሞርኩዞ የሚሰጥ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጡ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ምክንያቱን የሚጠቁሙ ተገቢ ሰነዶችን ከማቅረብ በተጨማሪ COSA ቅጽ ሞልተው ለ COSA ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት። COSA ቅጽ ተማሪው(ዋ) ለተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት መቅረብ አለበት። በሁሉም ት/ቤቶች የማይገኙ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች በመቀበል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚደረጉ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከጁላይ 1 በኋላ ይደረጋሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ፦ Department of Special Education Services at 850 Hungerford Drive, Room 230, Rockville, Maryland 20850 ይጠይቁ ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-3900 ያነጋግሩ።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥራ ባልደረቦች ተማሪዎች COSA በቀጥታ ይፈቀድላቸዋል?**

አይደለም። ይሁን እንጂ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስትራቴጂያዊ የቅድሚያ ትኩረት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ በ "Title I ትምህርት ቤቶች" በኢኖቬሽን የትምህርት ቤት የቀን መቁጠሪያ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም በፎከስ ትምህርት ቤቶች የሚሠሩ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ለማበረታታትና ለመደገፍ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ላይ የሚሠሩ ሠራተኞች በሚከተሉት ሁኔታዎች በሚሠሩበት ትምህርት ቤት እንዲሠማሩ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፦

a. ሰራተኛው(ዋ) ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ከላይ ከተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በአንዱ እንዲሰራ/እንድትሠራ የሚመደበው/የምትመደበው በጀት በተመደበበት የሙሉ ጊዜ ተመጣጣኝ (FTE) የስራ መደብ ላይ ሲሆን እረፍት ለመውሰድ፣ የጡረታ እና የጤና መድን ጥቅማጥቅሞች ሽፋን ለማግኘት ብቁ በሆነ(ች) በት የሥራ መደብ ላይ ነው።

b. የስራ ባልደረባው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ መሆን አለበ(ባ)ት፣ እና ተማሪው(ዋ)ም በሌላ መንገድ MCPS ለመመዝገብ ብቁ መሆን አለበ(ባ)ት፣ እና

c. ጥያቄውን የሥራ ባልደረባው(ዋ) በስራ ቀን በሁሉም ጊዜያት በሥራ ላይ ሲሆን/ስትሆን ከልጆች እንክብካቤ እቅድ ጋር አብሮ መቅረብ ይኖርበታል።

ሰራተኛዉ(ዋ) በሚሠራበት/በምትሰራበት ትምህርት ቤት የተማሪው(ዋ) መመደብ ሰራተኛው(ዋ)ን ስራዉን(ዋ)ን አጥጋቢ በሆነ መንገድ የማከናወን ችሎታዉ(ዋ)ን የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ የተማሪ ዝውውሩ እንደገና ሊታገድ ይችላል።

በዚህ ክፍል ከተገለፁት ትምህርት ቤቶች በአንዱ የማይሰሩ የ MCPS ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ እና ተዛማጅ ህጎች መስፈርቶች መሰረት ለልጆቻቸው COSAs ማመልከት ይችላሉ።

**የዝውውር ሂደቱ ለጥንድ የአንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንተሪ ት/ቤቶችም ተመሳሳይ ነው ወይ?**

አዎን። ተማሪው(ዋ) COSA የፀደቀ ጣምራ የትምህርት ፕሮግራም ቤል ፕሬ፣ ሞንትጎመሪ ኖልስ፣ ኒው ሃምፕሻየር ኢስቴትስ፣ ሮስኮ አር. ኒክስ፣ ሮዝማሪ ሂልስ እና ታኮማ ፓርክ ኤለመተሪ ትምህርት ቤቶች የሚከታተል/የምትከታተል ከሆነ(ች)፣ ላእላይ የኤለመንተሪ ት/ቤት ክፍሎች ለመግባት እንዲፀድቅላቸው COSA ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

**ወደ ፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት የተመደቡ እና ሞነከሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት ለመከታተል የሚፈልጉ ተማሪዎች አካሄዱ እንዴት ነው?**

ወላጆች/ሞግዚቶች እንዲፀድቅላቸው COSA ቅጽ ማቅረብ አለባቸው።

**COSA ለአካደሚክ ትምህርት፣ ለሲግኔቸር ፕሮግራሞች፣ ወይም ለልዩ ኮርሶች ይፈቀዳል?**

አይፈቀድም። ለሲግኔቸር ፕሮግራሞች እና ልዩ ኮርሶች የተተለሙት ለሚገኙበት ት/ቤት ነው። ወደነዚህ ት/ቤቶች የሚደረጉ COSA ጥያቄዎች ከሁሉም ሌሎች COSA ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። COSA ሂደት ነፃ ስለሆኑ ፕሮግራሞች የዚህን የመረጃ መጽሔት/ቡክሌት ገጽ 4-5 ይመልከቱ

**ተማሪዎች ለአካዳሚያዊ ዝውውር COSA ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ?**

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሚከተሉት በአንዱ ለመሣተፍ አካዳሚያዊ ዝውውር ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ:-

1. በዲስትሪክቱ ወይም በትምህርት ቤት የኮርስ ካታሎግ ዝርዝር ውስጥ እንደተገለጸው በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት ውስጥ የማይገኙ ተዛማጅ የሆኑ በተከታታይ ብዙ ዓመት ለሚወሰዱ ኮርሶች። ይህ ተዛማጅነት ያላቸው ኮርሶችን ቅደምተከተል ነውሙያዊ የጥናት ፕሮግራም በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት የማይሰጡ የካፕስቶን ኮርስ እና/ወይም ፕሮግራም ማጠናቀቂያን የሚያመለክት ነው።

   ምሳሌዎች:-

   በባለ ሙያ የሚመራ (ፕሮፌሽናል) የምግብ ቤት/ሬስቶራንት ማኔጅመንት ፕሮግራም:- ተከታታዮቹ ኮርሶች የምግብ ቤት (ሬስቶራንት) ማኔጅመንት 1፣ የምግብ ቤት (ሬስቶራንት) ማኔጅመንት 2፣ እና ካፕስቶን ኢንተርንሽፕ ወይም ጣምራ ምዝገባን ያካትታሉ።

   CASE ፕሮግራም: የተዛማጅ ኮርሶች ቅደም ተከተል ስለ ግብርና መቅድም፣ ስነ ምግብ፣ እና ስለ ተፈጥሮ ሀብት የመግቢያ ትምህርት፣ የተፈጥሮ ሀብት እና ሥነ ምኅዳር/ኢኮሎጂ፣ ስለ አካባቢ ሳይንስ፣ እና የግብርና ምርምር እና ልማት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

2. በተማሪው(ዋ) አካባቢ ትምህርት ቤት የማይገኝ፣ በዲስትሪክቱ ወይም በት/ቤት የኮርስ ማውጫ ውስጥ እንደተገለፀው የበርካታ ዓመታት ተከታታይነት ያለዉ ነጠላ ኮርስ። ይህ በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ውስጥ የማይሰጥ ልዩ ትምህርት የላቀ ደረጃ ጥናትን የሚያስከትል የብዙ-ዓመት ኮርስ ቅደም ተከተልን ይመለከታል።

   ምሳሌዎች:-

   አረብኛ 1፣ አረብኛ 2፣ አረብኛ 3

   ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 1፣ ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 2፣ ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 3

ማሳሰቢያ:- በመጀመሪያው የት/ቤት ቀን መቅረብ አለበትፌብሩወሪ 2024እና የመጀመሪያው የት/ቤት ቀን ኤፕሪል 2024። አመልካቾች ቦታ ካለ ይፈቀድላቸዋል። የእህትማማች/ወንድማማች ግንኙነት አይሠራም። ተማሪው(ዋ) ፕሮግራሙን ለማቋረጥ ከወሰነ(ች)፣ ተማሪው(ዋ) ወደ አካባቢ ትምህርት ቤት ይመለሳል/ትመለሳለች። የተፈቀደላቸው/አፕሩቭ የተደረጉ ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ዝውውር ፖሊሲ (ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ:- ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jee.pdf)

**COSA መስፈርቶች ነፃ የሆኑ ፕሮግራሞች ይኖራሉ?**

የሚከተሉት ፕሮግራሞች የዝውውሩ አካል ያልሆኑ በማመልከቻ ሒደት ተደራሽነት ያላቸው ምሳሌዎች ናቸው። ነገር ግን፥ ሌላ የምልመላ መስፈርት ሊተገበር ይችላል።

- በኮ/ሎ ዛዶክ መግሩደር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአቪዬሽን እና ኤሮስፔስ
- በሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮሙኒኬሽን አርትስ ፕሮግራም
- በጆን ኤፍ. ኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በስፐሪንግብሩክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ካውንቲ አቀፍ ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአመራር ማሰልጠኛ ተቋም
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW የምህንድስና ፕሮግራም
- በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ፕሮግራም
- በአልበርት ኢንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቪዡዋል አርት ማእከል
- የጤና እንክብካቤ ሙያዎች— የባዮሳይንስ አካዳሚ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ቶማስ ኤዲሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- የመስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት በግሎባል ስተዲስ አካዳሚ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በቶማስ ኢድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ-አካደሚ ኦቭ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኢድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና ምህንድስና አካደሚ ኦቭ ኢንጅነሪንግ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በቶማስ ኤዲሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- መካከለኛ ደረጃ ኮሌጅ በኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሞንትጎመሪ ኮሌጅ MC2 ፕሮግራም
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ኢንጅነሪንግ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች

- የመስተንግዶ ማኔጅመንት IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -ኮምፒውተር ሳይንስ IB ሙያ ፕሮግራሞች
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቻይልድ ደቨሎፕመንት አሶሽዬት IB የሙያ ፕሮግራሞች
- በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ግሎባል ኢኮሎጂ
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስለ ሰብአዊነት (ሑማኒቲስ)
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጤና ጥበቃ ሙያ
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ በ ሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና አርኪቴክቸር
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ ኢንጅነሪንግ
- በኖርዝዌስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሞንትጎመሪ ኮሌጅ መካከለኛ ደረጃ ኮሌጅ (MC2) ፕሮግራም
- በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ
- በክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኔትዎርክ ኦፐሬሽንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (PTECH)
- ሰብአዊነት - ሑማኒቲስ እና ኮሙኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራም በኢስተርን ሚድል ስኩል እና ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር ሚድል ስኩል
- በታኮማ ፓርክ ሚድል ስኩል እና ሮቤርቶ ክለመንቴ ሚድል ስኩል ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ እና ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም
- የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም (አርጋይለ፣ ሎኢ.ደርማን፣ ፓርክላንድ)
- ጠንካራ የዳበረ ትምህርት ጥናት ማእከሎች
- በማንኛውም የኤሌሜንታሪ ወይም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም የተመደቡ ተማሪዎች
- በት/ቤቶች ሱፐርኢንተደንት የሚለዩ ሌሎች ፕሮግራሞች
- በዊትማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለ ማህበራዊ ፍትህ አመራር
- በሼርዉድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግብርና ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት
- በአማራጮች (OPTIONS) ላይ የተገለጹት ሌሎች ፕሮግራሞች፦ የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች መመሪያ (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/options)

COSA ለአካዳሚክ ሽግግር የተፈቀደላቸው ተማሪዎች ያንን ፕሮግራም ካቋረጡ ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመለስ ይጠበቅባቸዋል፦ (ይህን ድረገጽ ይመልከቱ፦ ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jee.pdf)

COSA ጥያቄዬን ካቀረብኩ በኋላ ምን ሊሆን ይችላል?

በአካባቢ ት/ቤት ርእስ መምህር/ት ከተፈረመበትና የመኖሪያ አካባቢ ከተረጋገጠ በኋላ፣ COSA ጥያቄ በዓመት ከ3,000 እስከ 4,000 ማመልከቻዎችን ወደሚቀበለዉ DPPAS ይተላለፋል። ውሳኔ ከመስጠቱ አስቀድሞ DPPAS መጣራት ያለባቸውን ነገሮች ያጠናቅቃል። የአካዳሚክ ዝውውር/ለውጥ የማድረግ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣ የፕሮግራም ጥያቄውን መተንተን እና ከቤተሰብ ጋር መገናኘት እንዲቻል COSA ወደ "Office of Teaching, Learning, and School" ይተላለፋል።

ጥያቄዬ መጽደቁን ወይም ውድቅ መደረጉን መቼ ነው የምሰማው?

DPAS ሰራተኞች እስከሜይ 24, 2024 ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች በፖስታ ለማሳወቅ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ።

ለልጄ COSA አንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ በየአመቱ ማመልከት ያስፈልገኛል?

COSA የተወሰነው ለአንድ ዓመት ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪው/ዋ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ/እርከን ለመሻገር ዝግጁ እስከሚ(ምት)ሆን ድረስ COSA ፕሮግራም መቆየት ይችላል/ትችላለች። COSA ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች COSA እንደገና ማመልከት ያለባቸው ሲሆን ከአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ውጪ በሌላ ትምህርት ቤት ለመማር ያለባቸውን ልዩ የሆነ ችግር ማረጋገጥ/ማሳየት አለባቸው።

ልጄ COSA ከተፈቀደለ(ላ)ት በኋላ እንደገና ውድቅ ሊደረግ ይችላል?

አንድ ርእሰመምህር COSA በተገቢው ምክንያት እንዲሰረዝ ሊጠይቅ ይችላል። ለምሳሌ፥ የዲሲፕሊን ጥሰት ወይም በትምህርት ላይ ያለመገኘት ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

በአዲሱ ት/ቤት ልጄ በት/ቤቶች የስፖርት ውድድር ለመጫወት ብቃት ይኖረዋል/ራታል?

በወቅቱ ከራሳቸዉ የመጋቢ ት/ቤት ዉጪ COSA የሚያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አትሌቲክስ እንዲቀርላቸው ካላመለከቱ በስተቀር፣ በአትሌቲክስ ከመሣተፋቸው አስቀድሞ ለአንድ የካለንደር ዓመት በአዲሱ ት/ቤት መከታተል አለባቸው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የአትሌቲክስ ዲፓርትመንትን በስልክ ቁጥር 240-740-5650 ይጠይቁ።

ወደ አዲሱ ት/ቤት ትራንስፖርት ይቀርባል ወይ?

አይደለም። የመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት የወላጅ/የሞግዚት ኃላፊነት ነው።

የኔ COSA ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ እንዴት አድርጌ ነው ይግባኝ የምለው?

ለ፦ OFFICE OF CHIEF OF DISTRICT OPERATIONSበኢሜል DivisionOfAppeals@mcpsmd.org, 850 Hungerford Drive, Room 43, Rockville, Maryland 20850 ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። የዲስትሪክቱ ኦፕሬሽኖች የሥራ ኃላፊ እንደ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሆኖ ያገለግላል። ይግባኙ ውሳኔው ከተገለጸበት ቀን በኋላ ባሉት 15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለዲስትሪክት ኦፕሬሽን ጽ/ቤት በጽሁፍ መድረስ አለበት። ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ያስፈለገበትን ምክንያት(ቶች) ይግባኙ ላይ መገለጽ ይኖርበታል። ይግባኝ ለመጠየቅ ተጨማሪ መረጃ መስጠት ላይኖርብዎት ይችላል፣ ነገር ግን ቢታይ ይጠቅመኛል የሚሉትን ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 240-740-4130 ይደውሉ። COSA ይግባኝ ላይ ውሳኔ የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት ይከታተላሉ።

ይግባኝ በሙሉ የሚታየው በቀረቡት ሠነዶች እና በክትትል ኮሚዩኒኬሽን/ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ነው።

ይግባኝዎ በዲስትሪክቱ ዋና ኃላፊ ውድቅ ከተደረገ፣ምንም እንኳን ማንኛውንም ይግባኝ በፍጥነት እንዲያቀርቡ በጥብቅ የሚበረታቱ ቢሆንም፥ የዲስትሪክቱ ኦፕሬሽን ኃላፊ ውሳኔ ደብዳቤ በተሰጠበት 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ በኢሜል boeappeals@mcpsmd.org፣ ወደ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። አድራሻ፦ 15 WEST GUDE DRIVE, ROOM 100, ROCKVILLE, MARYLAND 20850 ሁሉም ይግባኞች የሚሰሙት በቦርዱ መደበኛ የስብሰባ ቀኖች ነው። ቦርዱ በኦገስት ወር እረፍት ላይ እንደሚሆን እባክዎ ያስታውሱ።

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

MCPS ቅጽ 335-45
ጃንዋሪ 2024

# 2024–2025 የትምህርት ቤት ምደባ ለመቀየር የሚቀርብ ጥያቄ (COSA)

ለ 2024-2025 የትምህርት አመት የጥያቄ ማቅረቢያ ቅጾች ፌብሩዋሪ 2024 የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በፊት እና ከኤፕሪል 2024 የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በፊት መቅረብ አለባቸው። በልዩ ሁኔታ የሚታይ ካልሆነ በስተቀር፣ ዘግይተው የደረሱ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

የወረቀት ቅጽ የሚጠቀሙ ከሆነ እባክዎን ለመጻፍ ጥቁር ቀለም ይጠቀሙ።

ገለጻዎች፡ ወላጅ/አሳዳጊ የቅጹን ክፍል 1 በመሙላት ከኤፕሪል 2024 የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በፊት ቅጹን ለአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ማስረከብ ይኖርባቸዋል። ቅጹን ከመሙላትዎ በፊት በምድብ ትምህርት ቤት ዝውውር (Change of School Assignment (COSA)) የመረጃ ቡክሌት ላይ የሚገኘውን መረጃ በጥንቃቄ ያንብቡ። የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JEE፣ስለ ተማሪ ዝዉዉር፣ እና የ MCPS ደንብ JEE-RA፣የተማሪ ዝዉዉሮች እና አስተዳደራዊ ምደባዎች ይመልከቱ።

## የመጀመሪያ ክፍል I:- በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ.

የተማሪ ስም ______________________________ የልደት ቀን_____/_____/______
የመጨረሻ ስም የመጀመሪያ ስም የአባት ስም መነሻ ፊደል

የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ያገኛል/ታገኛለች? አይደለም ❑ አዎ ❑

አሁን በሚማርበት/በምትማርበት ት/ቤት ______________________________ በኦገስት 2024 የሚ(ምት)ገባበት ክፍል_______

የአካባቢ ት/ቤት______________________የተጠየቀው ት/ቤት______________________ተግባራዊ የሚደረግበት ቀን_____/_____/______

ወላጅ/አሳዳጊ:- ______________________________

አድራሻ/Address: ______________________________
Street City State Zip Code

የቤት ሥልክ_____-_____-______ የሥራ ቦታ ስልክ_____-_____-______ ሞባይል ስልክ_____-_____-______

ኢሜል አድራሻ ______________________________ ቤት ውስጥ የሚነገር ቋንቋ ❑ TTY ያስፈልጋል ✜✞

በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የተፈቀደዉ ትምህርት ቤት ከተማሪው/ዋ የመጋቢ ት/ቤቶች ክልል ውጭ መሆኑ ይገባኛል፡- 1) MCPS መጓጓዣ አያቀርብም፣ 2) ተማሪው/ዋ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከሆነ/ች፣ (እንዲሠረዝለ(ላ)ት ካልተፈቀደ በስተቀር) በአትሌቲክስ ለመሳተፍ ብቁ ከመሆኑ(ኗ) በፊት በአዲሱ ት/ቤት አንድ አመት መከታተል እንዳለበ(ባ)ት፣ እና 3) የተፈቀደዉ ት/ቤት ርእሰ መምህር ተገቢ በሆነ ምክንያት የተማሪው/ዋ COSA እንዲሰረዝ ሊጠይቅ/ልትጠይቅ ይችላል/ትችላለች። (MCPS ደንብ JEE-RA ይመልከቱ)።

በዚህ ቅጽ እና በማናቸውም አባሪዎች ላይ የቀረቡት መረጃዎች እኔ እስከማውቀው ድረስ ትክክለኛ፣ የተሟሉ እና እውነት ናቸው። ገቢ በተደረገ ማንኛዉንም መረጃ/ኢንፎርሜሽን ማጭበርበር ለ COSA ውድቅ መሆን ምክንያት እንደሚሆን ተረድቻለሁ።

ፊርማ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ______________________________ ቀን_____/_____/______

ጥያቄ የቀረበበት ምክንያት፡-

- ❑ የተለየ አስቸጋሪ ሁኔታ- እባክዎ በዝርዝር ይግለጹ፡- የማረጋገጫ ሰነድ/ማስረጃ ከዚህ ቅጽ ጋር አባሪ መሆን አለበት።
- ❑ የቤተሰብ ዝውውር—በቤተሰብ ዝውውር ምክንያት ይህንን የትምህርት ዓመት ለማጠናቀቅ ብቻ ነው።
- ❑ ወንድምና እህት—ወንድም/እህት በተጠየቀው ት/ቤት <> ክፍል ይማራል/ትማራለች፣ የወንድም/እህት ስም __________ የወንድም/እህት MCPS መታወቂያ ቁጥር # <>
- ❑ በ 2021–2022 የትምህርት ዘመን በኢመርዥን ፕሮግራም 3ኛ ክፍል ለገቡ እና ከመካከለኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በመጋቢ ት/ቤት መቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች እባክዎ ያስታውሱ፡ እስከ ስፕሪንግ/ፀደይ 2027 ድረስ ይሠራል።
- ❑ ለቤል ፕሪ፣ ሞንትጎመሪ ኖልስ፣ ኒው ሃምፕሻየር እስቴትስ፣ ሮስኮ አር.ኒክስ፣ ሮዝሜሪ ሂልስ እና ታኮማ ፓርክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ3ኛ—5ኛ ክፍል ጥምር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምደባ የመቀጠል ፍላጎት። (ቀደም ሲል የፀደቀ COSA ቅጽ ተሞልቶ ከቀረበ ወዲያውኑ ሊጸድቅ ይችላል)
- ❑ በፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት የተመደበ/ች ተማሪ በሞኖካሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት ለመማር የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነና COSA ቅጽ ካቀረበ(ች) ወዲያውኑ ሊፀድቅ/ተቀባይነት ማግኘት ይቻላል።
- ❑ የ MCPS ስራ ባልደረባ Title I ትምህርት ቤት፣ በኢኖቬቲቭ የትምህርት ካላንደር ትምህርት ቤት፣ ወይም የልዩ ትኩረት ትምህርት ቤት፣ የራሷ(ሱ) ልጅ በሚሠራበት/በምትሠራበት ትምህርት ቤት ተዛውሮ(ራ) እንዲማር ወይም እንድትማር ስለመጠየቅ። የተቀጠሩበት/የሚሠሩበት ትምህርት ቤት ስም። ______________________________
- ❑ የአካዳሚክ ለውጥ (ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ) የፕሮግራሙን ስም ያመልክቱ። ______________________________
  የግምገማው ሒደት በተጠየቀው ትምህርት ቤት የቦታ እና በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት የፕሮግራም መገኘት-አለመገኘትን ግምት ውስጥ ያስገባል።
- ❑ ከኤፕሪል 2, 2024 በኋላ ከገባ፣ እባክዎን ጥያቄው ከቀረበበት ቀን በኋላ የቀረበበትን ምክንያት የሚያብራራ ሰነድ ያቅርቡ።

## ሁለተኛው ክፍል II የትምህርት ቤት ግምገማ። በተማሪው/ዋ የአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር የሚሞላ።

የነዋሪነት ማረጋገጫ ተሟልቷል ቀን_____/_____/______ ት/ቤት #________ MCPS የተማሪ መታወቂያ ቁ #______________________________

ይህንን ጥያቄ በሚመለከት ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ተነጋግሬአለሁ አዎ ❑ አይደለም ❑ ለት/ቤት የቀረበበት ቀን_____/_____/______

ፊርማ፣ ርእሰመምህር ______________________________ ቀን_____/_____/______
(መፈረም ማለት በቀረበው ጥያቄ ላይ ስምምነትን/አለመስማማትን ለማረጋገጥ ሳይሆን ነገር ግን ነዋሪነቱ(ቷ) የተረጋገጠ መሆኑን ብቻ ያመለክታል።)

ወደ COSArequest@mcpsmd.org ተላልፏል፡-

## ሦስተኛው ክፍል III DPPAS ACTION/የተወሰደ እርምጃ። DPPAS አማካይነት የሚሞላ።

Forwarded to: Consortium Office ❑ Special Education ❑ Date _____/_____/______

**DPPAS Decision: ❑ Approved ❑ Approved, to the end of school year ________________ ❑ Denied—Does not meet criteria**

**❑ Denied—Submitted after deadline, absent of emergency circumstances**

Comments: ______________________________

Signature, Director or Coordinator, DPPAS ______________________________Date _____/_____/______

**ይግባኝ፡-** ይግባኙ DPPAS ተቀባይነት ካላገኘ፣ (እባክዎ ምክንያቱን እና ማንኛዉንም ተጨማሪ መረጃ ይግለጹ) ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ 15 የካላንደር ቀናት ውስጥ ለ..በፅሁፍ መቅረብ አለበት፡- Chief of District Operations, Montgomery County Public Schools, 850 Hungerford Drive, Room 43, Rockville, Maryland 20850, 240-740-4130, Divisionofappeals@mcpsmd.org.

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ሕትመት፡- Department of Materials Management for the Chief of District Operations
ትርጉም፡- በኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ጽ/ቤት የቋንቋዎች ድጋፍ አገልግሎት ክፍል
Language Assistance Services Unit • Office of Communications
0583.24ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 1/24 • NP
Copyright © 2024 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland